ለወላጆችና የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች የተዘጋጀ መምሪያ

# በሜሪላንድ ውስጥ ያለውን የግምገማ፣ የብቁነትና የግል ትምህርት መርሃ ግብር (IEP) ሂደቱን መረዳት



MARYLAND STATE DEPARTMENT OF EDUCATION
Achievement Matters Most

የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ
የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች (Division of Special Education/Early Intervention Services)

12/2008 ቀን ተሻሻለ

# ማውጫ፡-

**መግቢያ** 2
የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎቶች 3
ለቤተሰቦች ተጨማሪ ጠቃሚ ዘዴዎች 4
**የአካል እና የአእምሮ ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎችን ለይቶ ማወቅ**
የመጀመሪያ ጥቆማ 6
ምርመራ እንደሚያስፈልግ መወሰን 6
ምርመራዎች 6
ግምገማ 7
የመጀመሪያ ግምገማ 8
የመጀመሪያ ግምገማን ለመጨረስ የሚያስፈልግ የጊዜ ገደብ 9
ደግሞ ግምገማ ማድረግ 9
የአገልግሎቶች ፍጻሜ 9
ከሕጻናት መርሃ ግብር ወደ ልጆች መርሃ ግብር መሸጋገር 10
**የግል ትምህርት መርሃ ግብር (IEP) ሂደት**
የIEP ቡድን ስብሰባዎች 10
ስብሰባዎች ውስጥ የወላጅ ተሳትፎ 11
የIEP ቡድን 12
የIEP ቡድን በቦታው መገኘት 13
የIEP ይዞታ 13
የሽግግር አገልግሎቶች 14
አፈጻጸም ባጭሩ 15
ለልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ፈቃድ መስጠት 15
ለልዩ ትምህርት አገልግሎቶች የተሰጠን ፈቃድ መሰረዝ 15
IEP እድገት፣ ግምገማና እና ክለሳ 16
ማሻሻያ ነጥቦች 17
ምደባ 17
IEPን ተግባር ላይ ማዋል 18
ወደ ሌላ የመንግሥት ድርጅት ስለሚዛወሩ ልጆች 18
የምረቃ አስፈላጊ ጉዳዮች 19
የተራዘመ የትምህርት ዓመት አገልግሎቶች (ESY) 19

# መግቢያ፡-

ይህ የሜሪላንድ ግምገማ፣ የብቁነትና የIEP ሂደቶችን መረጃ መምሪያ የተዘጋጀው በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ (Maryland State Department of Education (MSDE)) ሲሆን፣ ስለ ልጅዎ መብቶች፣ ስለራስዎ መብቶችና ኃላፊነቶች እና ልጅዎ የሚያስፈልገውን ልዩ ጥንቃቄዎች ስለማሟላት ትምህርት ቤቱ ያለበትን ኃላፊነት በተመለከተ በይበልጥ ግንዛቤ እንዲኖርዎት የተዘጋጀ ነው። ይህ መምሪያ ስለ Child Find፣ ስለ ግምገማ፣ ብቁነትና የግል ትምህርት መርሃ ግብር (IEP) ሂደቶች ማብራሪይ ይዟል።

ልጆች በትምህርት በይበልጥ ጎበዝ የሚሆኑት ቤተሰቦቻቸው በእድገታቸውና በትምህርታቸው በይበልጥ ተሳትፎ ሲያሳዩ እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ። የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ላለበት ልጅ የወላጅ ተሳትፎ እንዲየውም በይበልጥ አስፈላጊ ነው። ብዙ ጊዜ፣ ስለ አንድ ልጅ ጠንካራ ጎኖች በይበልጥ መረጃ መስጠት የሚችሉት ወላጆች ብቻ ሲሆኑ፣ ጉዳት ሲኖር የልጁን የመማር ችሎታ ወይም እድገት ላይ ተጽእኖ እንዴት እንደሚኖረውም እነሱ ናቸው መናገር የሚችሉት። ወላጆች የልጆቻቸው ትምህርት ላይ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። ለልጆች ተገቢውን የትምህርት አገልግሎቶች ለመስጠት፣ ወላጆችና የትምህርት ቤቱ ሠራተኞ አብረው እንዲሠሩ ሕጉ ይጠይቃል። ጉዳት ያለበት የልጅ ወላጅ እርዳታ ካስፈለገው/ካስፈለጋት ጥያቄ መጠየቅ ወይም እርዳታ መጠየቅ አለበት/አለባት።

የ MSDE የልዩ ትምህርት/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ክፍል፣ ሶስት ክፍል ያለው የአካባቢው ወላጅ ድጋፍ አስተባባሪዎች አውታር የያዘ ሲሆን፣ እነዚህም አስተባባሪዎች ዕድሜያቸው ከሕጻን እስከ 21 ዓመት ድረስ ያሉ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያለባቸውን ልጆች ወላጆች ልጆቻቸው ተገቢውን ልዩ ትምህርት እንዲያገኙና ለልጆቻቸው ቅድመ ጣልቃ ገብ አገልግሎቶች የማግኛ ሂደት ላይ ይረዳሉ። እያንዳንዱ የሜሪላንድ አውራጃ ለሚከተለሉት የዕድሜ ቡድኖች የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ላላቸው ልጆች የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎቶች አስተባባሪዎች አሏቸው፡-

- ከተወለዱ እስከ 3 ዓመት ዕድሜ ድረስ - Family Support Network
- ከ3 ዓመት እስከ 5 ዓመት ዕድሜ ድረስ — Preschool Partners
- ከ5 ዓመት እስከ 21 ዓመት ዕድሜ ድረስ — Partners for Success

እነዚህ አስተባባሪዎች ቅድመ ጣልቃ ገብነትና የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን ጉዳይ ለመወያየት፣ በቤተሰቦች መካከል አዲስ ግንኙነት ለመፍጠር፣ መረጃ ለመስጠትና የመዋሻ ላይብረሪዎችን ለማስተናበር፣ የወላጅ ስልጠና መስጫና የድጋፍ ቡድኖችን ለማስተናበር እንዲሁም ጥያቄዎችን ለመመለስ ይገኛሉ። እንዲሁም ወላጆች ከትምህርት ቤቶች ጋር አለመግባባት ሲያጋጥማቸው ኦፊሲዬላዊ ያልሆነ እርዳታ ለወላጆች በማቅረብ ወይም በ2004 ዓ.ም. የወጣው የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ማሻሻያ ሕግ (Individuals with Disabilities Education Improvement Act of 2004 (IDEA)) ውስጥ ያሉትን የግጭት መፍቻ ሂደቶችን

በተመለከተ መረጃ ለወላጆች ያቀርባሉ።

በሚቀጥለው ገጽ ላይ በአውራጃዎ የሚገኙትን የቤተሰብ ድጋፍ አስተባባሪዎች ዝርዝር ያገኛሉ። አስተባባሪዎቻችን ሁሉ ጉዳት ያለባቸውን ልጆች ለማገልገል ከእርስዎ ጋር አብሮ ለመሥራት በጉጉት ይጠብቃሉ።

# የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎቶች

## የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያለባቸው ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች፦

### በአካባቢው የሚገኙ የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎት አስተባባሪዎች ማውጫ

| አውራጃ | ከሕጻን እስከ 3 ዓመት ዕድሜ ድረስ Family Support Network | ዕድሜያቸው ከ3 ዓመት እስከ 5 ዓመት PreschoolPartners | ዕድሜያቸው ከ3 ዓመት እስከ 21 ዓመት Partners For Success |
|---|---|---|---|
| አሌጋኒ ካውንቲ | 301-689-2407 | 301-689-2407 | 301-689-2407 |
| አን አሩንዴል ካውንቲ | 410-222-6911 | 410-222-3805 | 410-222-3805 |
| ባልቲሞር ከተማ | 410-396-1666 | 410-396-8995 | 410-396-8995 |
| ባልቲሞር ካውንቲ | 410-887-2169 | 410-887-5443 | 410-887-5443 |
| ካልቨርት ካውንቲ | 410-535-7387 | 410-535-7387 | 410-535-7387 |
| ካሮላይን ካውንቲ | 410-479-4204 | 410-479-4204 | 410-479-4204 |
| ካሮል ካውንቲ | 410-876-4437 | 410-751-3955 | 410-751-3955 |
| ሴሲል ካውንቲ | 410-996-5637 | 410-996-5637 | 410-996-5637 |
| ቻርልስ ካውንቲ | 301-934-7456 | 301-934-7456 | 301-934-7456 |
| ዶርቼስተር ካውንቲ | 410-221-0837 | 410-221-0837 | 410-221-0837 |
| ፍሬድሪክ ካውንቲ | 301-600-1617 | 301-600-1617 | 240-236-8430 |
| ጋሬት ካውንቲ | 301-334-8119 | 301-334-8119 | 301-334-8935 |
| ሃርፈርድ ካውንቲ | 410-638-3823 | 410-638-3823 | 410-273-5579 |
| ሃወርድ ካውንቲ | 410-313-7161 | 410-313-7161 | 410-313-7161 |
| ኬንት ካውንቲ | 410-778-5708 | 410-778-5708 | 410-778-5708 |
| ሞንትጎመሪ ካውንቲ | 240-777-4809 | 240-777-4809 | 301-279-3100 |
| የፕሪንስ ጆርጅ ካውንቲ | 301-883-7428 | 301-883-7428 | 301-431-5675 |
| የክዊን አን ካውንቲ | 410-827-4629፣ ኤክስቴንሽን 149 | 410-827-4629 | 410-758-3693 |
| ሶመርሲት | 410-651-9413 | 410-651-9413 | 410-651-9413 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ካውንቲ | | | |
| የሴንት ሜሪ ካውንቲ | 301-475-4393 | 301-475-4393 | 301-863-4069 |
| ታልበት ካውንቲ | 410-820-7468 | 410-820-7468 | 410-820-7468 |
| ዋሽንግተን ካውንቲ | 301-766-8221 | 301-766-8221 | 301-766-8221 |
| ዊኮሚኮ ካውንቲ | 410-677-5250 | 410-677-5250 | 410-677-5250 |
| ዎርሴስተር ካውንቲ | 410-632-5234 | 410-632-5234 | 410-632-5234 |

### የስቴቱ የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎት አስተባባሪዎች

| | |
|---|---|
| Maryland State Department of Education Family Support Services (የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎቶች - ለሜሪላንድ ወታደር ቤተሰቦችና የታሰሩ ወይም ወህኒ ቤት የገቡ ወጣቶች ቤተሰቦች ድጋፍን ጨምሮ) | 1-800-535-0182 |
| Maryland School For the Blind (የሜሪላንድ አይነ ስውራን ትምህርት ቤት) | 1-800-400-4519 ኤክስቴንሽን 489 |
| Maryland School For the Deaf (የሜሪላንድ መስማት የሚሳናቸው ትምህርት ቤት) | 410-480-4597 |

ሙሉ ማውጫ ኢንተርኔት ላይ በሚከተለው አድራሻ ይገኛል፦ www.mdecgateway.org

# ተጨማሪ ጠቃሚ መረጃዎች

## የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያላቸው ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች፦

• Maryland State Department of Education (የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ)
http://marylandpublicschools.org/msde
ስለ ሜሪላንድ ስቴት ትምህርት መምሪያና የሜሪላንድ መንግሥት ትምህርት ቤቶች እንቅስቃሴዎች፣ የሜሪላንድ ቮለንቴሪ ስቴት ከሪክዩለም ግምቶችን ጨምሮ።

• Maryland State Department of Education
Division of Special Education/Early Intervention Services (የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ የልዩ ትምህርት/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ክፍል)
http://marylandpublicschools.org/msde/divisions/earlyinterv/
ስለ ኦቲዝም፣ ከሜሪላንድ ቤተሰቦች ጋር IEPዎችን ስለመገንባት፣ የስቴቱ በሙሉ IEP ቅጽና ፎርማት፣ አለመግባባትን ስለመፍታት መረጃዎችና ሌሎችም።

• Maryland Early Childhood Gateway (የሜሪላንድ እርሊ ቻይልድሁድ ጌትዌይ)

http://ww.mdecgateway.org
ዕድሜያቸው ከሕጻን እስከ አምስት ዓመት የሆኑ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ላለባቸው ልጆች ቤተሰቦችን ዶክተሮቻቸው ኢንተርኔት ላይ የሚገኝ መረጃ።

- የሂደት ማስከበሪያዎች
  ይህ መምሪያ የሥርዓታዊ መከላከያ ሰነድን ወይም ማንኛውንም አስፈላጊ ማስታወቂያ ለመተካት የታሰበ አይደለም፣ የስቴቱን ልዩ ትምህርት ደንቦችም መተኪያ አይደለም። ሕጋዊ መብቶችዎን በይበልጥ መረዳት እንዲችሉ፣ በሂደቱ ወቅት በተወሰኑ ጊዜዎች ላይ ትምህርት ቤቶቹ ለወላጆች የሥርዓታዊ መከላከያ ሰነዱን ቅጂ ይሰጣሉ፣ አርእስቱም የወላጆች መብቶች - ሥርዓታዊ መከላከያ ማስታወቂያ የሚል ይሆናል። የወላጆች መብቶች - ሥርዓታዊ መከላከያ ማስታወቂያን በኮምፒዩተር ለማግኘት የሚከተለውን ዌብሳይት ይጉብኙ፦ www.marylandpublicschools.org/MSDE/divisions/earlyinterv/Special_Ed_Info.htm.

- Code of Maryland Regulations (COMAR) (የሜሪላንድ ደንቦችና ሥርዓቶች)
  The State Division of State Documents Web site provides access to the Code of Maryland Regulations: http://www.dsd.state.md.us/comar/.

- U.S. Department of Education (የዩኤስ ትምህርት መምሪያ)
  የዩናይትድ ስቴትስ ትምህርት መምሪያ የጉዳተኛ ግለሰቦችን የትምህርት ሕግ (Individuals with Disabilities Education Act) በተመለከተ በሚከተለው ዌብሳይት ላይ መረጃ ይሰጣል፦ http://idea.ed.gov/.

# ጉዳት ያለባቸውን ልጆች ለይቶ ማወቅ፦

ቻይልድ ፋይንድ (Child Find) የተባለው ጉዳት ያለባቸውን ተማሪዎች መለያ ሂደት፣ ትምህርት ቤቶችና የመንግሥት ድርጅቶች የሚጠቀሙበት፣ ዕድሜያቸው ከ ሶስት እስከ 21 ያሉ ልዩ ትምህርት የሚያስፈልጋቸው ልጆችን የሚለዩበት መንገድ ነው። ሜሪላንድ በስቴቱ ውስጥ የሚኖሩ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያለባቸው ልጆች በሙሉ፣ የግል ትምህርት ቤት የሚሄዱትን ጨምሮ፣ የአካል ጉዳታቸው መጠን ከባድም ይሁን ቀላል፣ ልዩ ትምህርትና ተያያዥ አገልግሎቶች የሚያስፈልጋቸውን ልጆች ለይቶ፣ ቦታቸውን አውቆ ግምገማ እንዲያገኙ አድርጎ ልዩ ዘዴ በመጠቀም የትኞቹ ልዩ ትምህርትና አገግሎቶች እያገኙ እንደሆነ ለማወቅ የሚያስችሉት ደንቦችና ሥርዓቶች በሥራ ላይ ያውላል። ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፦

- በአካባቢው ያለው የትምህርት ሥርዓት ውስጥ የሚገኝ የግል አንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ፣ እንዲሁም ቻርተር ትምህርት ቤቶች የሚሄዱ ልጆች፣
- ከቦታ ቦታ ብዙ የሚንቀሳቀሱ ልጆችና ከውጪ የሚመጡ ልጆች፣
- ቤት አልባ ልጆች፣

- በስቴቱ አስተዳደግ ሥር ያሉ ልጆች፣ እና
- የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት አለባቸው ተብለው የሚጠረጠሩ ልጆች፣ ምንም እንኳን ከአንድ ክፍል ወደሚቀጥለው እያለፉ ያሉ ቢሆኑም።

## የመጀመሪያ ጥቆማ፦

አንድ ወላጅ ወይም አንድ የትምህርት ቤት ተቀጣሪ በማንኛውም ጊዜ የአንድ ተማሪን ግምገማ ለማግኘት ሲፈልግ፣ ለተማሪው ዋና ዳይሬክተር ወይም ለአካባቢው ልዩ ትምህርት አስተዳዳሪ በጽሑፍ ጥያቄ አቅርቦ ማግኘት ይችላል። በጽሑፍ የሚያቀርቡት ጥያቄ ጥቆማዎን በጽሑፍ ያስመዘግብና የጊዜ ገደቡን ይጀምራል። ጠቋሚው ግምገማ የተጠየቀባቸውን ምክንያቶች አስረድቶ ጉዳዮቹን ለመከታተል የተደረጉ ሙከራዎች ካሉ እነርሱን ማብራራት አለበት።

የመንግሥት ድርጅቱ ግምገማዎች አስፈላጊ ናቸው ብሎ ከወሰነ፣ ልጅዎ ልዩ ትምህርትና ተያያዥ አገልግሎቶች እንደሚያስፈልገው/እንደሚያስፈልጋት ለመወሰን የሚያስችል ግምገማ ከማድረጉ በፊት ከእርስዎ ፈቃድ መጠየቅ አለበት። እርስዎ በጽሑፍ ፈቃድ ሳይሰጡ አንድ የመንግሥት ድርጅት ልጅዎ ላይ ግላዊ ግምገማ ማኪያሄድ አይችልም። አንድ የመንግሥት ድርጅት መዝገብ ላይ ያለ መረጃ ለማየት ወይም ለሌሎች ልጆች በሙሉ የሚሰጥ ፈተና ለልጅዎ ከመስጠቱ በፊት ፈቃድ ማግኘት የለበትም፣ ከልጆች ወላጆች በሙሉ ፈቃድ ካላስፈለገ በስተቀር። አንድ የመንግሥት ድርጅት ልጅዎ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ስላለበት/ስላለባት ልዩ ትምህርት ያስፈልገዋል/ያስፈልጋታል ብሎ አምኖ በጽሑፍ ፈቃድ ለመስጠት ካልተስማሙ፣ የመገላገያ ውይይት ላይ ወይም ችሎት ፊት እንዲቀርቡ ድርጅቱ ሊጠይቅዎ ይችላል። የተማሪው ወላጅና የ IEP ቡድን በጽሑፍ በቀረበ ስምምነት መሠረት የጊዜ ገደቡን ካላራዘሙት በስተቀር አንድ የመንግሥት ድርጅት የሜሪላንድ ደንቦችና ሥርዓቶች (COMAR) ውስጥ የተጠቀሰውን የጊዜ ገደብ ማክበር አለበት።

## ግምገማ እንደሚያስፈልግ መወሰን፦

የመንግሥት ድርጅቱ የግምገማ ሥርዓቶች እንዳስፈላጊነታቸው መኪያሄዳቸውንና ማንኛውም የመንግሥት ድርጅቱ ለማድረግ የሚፈልገውን ወይም ለማድረግ ፈቃደኛ ያልሆነውን ግምገማ በጽሑፍ ለወላጆች ማሳወቁን ያረጋግጣል። የመንግሥት ድርጅቱ ተጨማሪ መረጃ አያስፈልግም ብሎ ከወሰነ ወይም ልጅዎ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት አለበት ብሎ ካልጠረጠረ፣ ልጅዎን ለመገምገም ያልተስማማበትን በጽሑፍ አቅርቦ ለእርስዎ መስጠት አለበት። በውሳኔው ካልተስማሙ የአስተዳደር ችሎት ቢሮ ጋር (Office of Administrative Hearings (OAH)) ይግባኝ ማለት ይችላሉ።

## ምርመራዎች፦

ምርመራዎች ለእያንዳንዱ ተማሪ ለግሉ እንዲሆኑ ሆነው የተሠሩ ናቸው። አንድ የመንግሥት ድርጅት የተለያዩ የመገምገሚያ መንገዶች እና ዘዴዎች ተጠቅሞ አስፈላጊውን የልጁን የአሠራር፣ የእድገት እና የትምህርት መረጃ መሰብሰብ ይችላል። ይህ መረጃ ልዩ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳተኛ መሆኑን ለመገምገም ሊረዳ ይችላል፣ የልጁንም IEP በዚህ መገምገም ይቻላል። የትምህርት መረጃው የልጅዎን አጠቃላይ

የትምህርት ይዞታ እንቅስቃሴን ያካትታል፣ መዋለ ሕጻናት ያለ ልጅ ከሆነም ተገቢዎቹ እንቅስቃሴዎች ላይ ያለውን ተሳትፎ ያሳያል። ግምገማዎች የሚያጠቃልሉት የወረቀት ፈተናዎችን፣ ማስተዋሎችን፣ ከወላጆች የተገኘ መረጃን እንዲሁም የሚከተሉትን ዓይነት መረጃዎችን ይጨምራል፦

- የተወሰኑና በዘር ወይም በባህል ተጽእኖ በማያሳይ ሁኔታ የሚሰጡ፣
- የማይቻል ካልሆነ በስተቀር፣ በልጁ የትውልድ ቋንቋ ወይም በይበልጥ ትክክል ውጤት በሚያስገኝበት የመግባቢያ ሌላ መንገድ የሚሰጡ ልጁ በትምህርቱ ላይ፣ በእድገት በኩልና በአሠራሩ ያለውን እውቀት የሚፈትኑ፣
- ግምገማዎቹና መመዘኛዎቹ ለሚሠሩበት ምክንያት የሚጠቀሙባቸው፣ የሚሰጡትም ሥልጠና ባገኙና እውቀቱ ባላቸው ሠራተኞች፣ የፈተናው አቀነባባሪ በሚሰጠው መምሪያ መሠረት የሚሰጡ፣
- የተወጠነው በተወሰኑ አርእስቶች ላይ ያለውን ትምህርት ነክ አስፈላጊ ነገር ለማወቅ እንጂ በአንድ ነጥብ የማሰብ ችሎታን ለመገምገም አይደለም፣ እንዲሁም
- የተመረጠው የልጁን ትክክለኛ ብቃት ወይም የፈጸመውን ሥራ ለማሳየት እንጂ ጉዳት ያለውን ሕዋስ፣ የእጅ ሥራ ወይም የመናገር ችሎታ አይደለም፣ ፈተናው የሚመዝነው እነዚህን ካልሆነ በስተቀር።

እያንዳንዱ የግምገማ ሪፖርት የሚከተሉትን ያካትታል፦

- በእያንዳንዱ የተጠረጠረ ጉድለት ዙሪያ ልጁ እንዴት እንደሠራ ማብራርያ፣
- ተገቢ የአሠራር፣ የማዛመጃ፣ የእድገት፣ የባሕርይና የአካል መረጃ፣
- ልጁ በአጠቃላይ የትምህርት መርሃ ግብሩ ላይ ሲሳተፍ በትምህርት አሰጣጡ ላይ ሊያመጣ የሚችለውን ነገሮች ወይም የመዋለ ሕጻናት ዕድሜ ልጅ ከሆነ ተገቢዎቹ እንቅስቃሴዎች ላይ፣ እንዲሁም
- በመደበኛ ሁኔታዎች ሥር ላይተሰጡ ግምገማዎች በሙሉ ከመደበኛ አስተዳደር ሂደት እንዴት እንደሚለዩ የሚገልጽ ማብራሪያ።

## <u>ግምገማ፦</u>

ግምገማ ማለት በፌዴራልና በስቴት የግምገማና የብቃት መለኪያ ደንቦች መሠረት የሚደረጉ ሂደቶች ሲሆኑ፣ አንድ ልጅ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያለበት መሆኑን መገምገሚያና ምን ዓይነት ትምህርት እንደሚያስፈልገው ማወቂያ ነው። በIDEA ሥር የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳተኛ የሆነ ልጅን የመጀመሪያ ልዩ ትምህርት ከመሰጠቱ <u>በፊት</u> የተሟላና የግል ግምገማ ይሰጠዋል። ግምገማ የሚኪያሄደው የ IEP ቡድኑ ሲሰበሰብ እና እንደ አግባብነቱ ሌሎች ባለሙያዎች ተገኝተው የሚከተሉትን ለመገምገም ነው፦

- ነባር መረጃና የግምገማ ውጤቶች፣
- ወላጆች የሚያመጡት ግምገማዎች እና መረጃ፣
- ወቅታዊ ክፍልን መሠረት ያደረጉ ግምገማዎች፣ የስቴትና የአውራጃ ግምገማዎችንና ግንዛቤዎች፣ እንዲሁም

- የሚከተለቱን ለመወሰን በአስተማሪዎችና ተዛማጅ የአገልግሎት ሠራተኞች የተደረጉ ግንዛቤዎች፦
  - ልጁ ጉዳት ያለበት ተማሪ መሆኑን ለማወቅ፣
  - የልጁ የሚያስፈልገው የትምህርት ዓይነት፣
  - ወቅታዊ የትምህርት ግፊትና ለእድገት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች፣
  - ልጁ የሚያስፈልገው ልዩ ትምህርትና ተያያዥ አገልግሎት፣ ልጁ አለበት ተብሎ ከተመደበበት የጉዳት ቡድን ጋር የተያያዘ ቢሆንም ባይሆንም፣ እንዲሁም
  - ልጁ የ IEPን እንዲሁም ካስፈለገ የአጠቃላይ ትምህርቱን ግቦች እንዲመታና አጠቃላይ የትምህርት ገበታው ላይ መሳተፍ የሚያስችሉት ተጨማሪ ነገሮችና ለውጦች።

## የመጀመሪያ ግምገማ፦

የመጀመሪያው ግምገማ ልጁ አለበት ተብሎ የሚጠረጠሩትን ጉድለቶች በሙሉ የሚመረምር አጠቃላይ ግምገማ መሆን አለበት። ተገቢ ከሆነም የሚከተሉትን ማካተት አለበት፦

- የትምህርት ብቃት
- ንግግር/መግባባት
- አጠቃላይ እውቀት
- ጤና፣ የመስማትና የማየት ችሎታን ጨምሮ
- ቴክኒካል ችሎታዎች
- ማህበራዊ፣ ስሜታዊና የባህርይ ሁኔታ

አንድ ልጅ ጉዳት ያለበት ተማሪ መሆኑን/መሆኗንና የትኛው ትምህርት ለልጁ/ለልጅቷ ተገቢ መሆኑን ለመወሰን የሚጠቀሙበት አንድ ብቸኛ ሥርዓት የለም።

የተወሰነበት መንገድ ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ከሆነ፣ አንድ ልጅ ጉዳት አለበት ስለዚህም ልዩ ትምህርት ያስፈልገዋል ማለት አይቻልም፦

- ተገቢው የማንበብ ትምህርት ሳይሰጥ በመቅረቱ፣ የምንባብ ትምህርትን ዋና ክፍሎች ጨምሮ፣ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፦
  - የፎኔሚክ እውቀት
  - ፎኒክስ
  - የቃላት እውቀት መዳበር
  - በየማንበብ ችሎታ፣ ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብን ጨምሮ
  - አንብቦ የመረዳት ዘዴዎች
- የሒሳብ ትምህርት ሳይሰጥ ቀርቶ
- የልጁ በቂ እንግሊዝኛ ቋንቋ አለመናገር፣ ልጁ ጉዳት ያለበት ልጅ ነው ተብሎ ካልተረጋገጠ በስተቀር።

## የመጀመሪያ ግምገማን ለመጨረስ የሚያስፈልግ ጊዜ ገደብ፦

የልጁ ወላጆች ወይም የመንግሥት ድርጅቱ ልጁ ጉዳት ያለበት መሆኑን ለማረጋገጥ የመጀመሪያ ግምገማ እንዲደረግላቸው መጠየቅ ይችላሉ። የመጀመሪያ ግምገማ ልጁን ለመገምገም ወላጆች የጽሑፍ ፈቃድ ከሰጡበት ቀን እስከ 60 ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ አለበት። የ60 ቀን የጊዜ ገደቡ በሚከተሉት ሁኔታዎች ጊዜ የአካባቢው የትምህርት ድርጅትን አይመለከትም፦

- ወላጆች ሌላ የመንግሥት ድርጅት ጋር ለመጀመሪያ ግምገማ ፈቃድ ከሰጡ በኋላ ግን ድርጅቱ ልጁ ጉዳት እንዳለበት ከመገምገሙ በፊት የመንግሥት ድርጅቱ በሚያገለግለው ትምህርት ቤት ውስጥ ልጁ ቢመዘገብ። ይህ የሚሆነው የመንግሥት ድርጁት ግምገማው እንዲያልቅ በቂ እርምጃ እያደረገ ከሆነና ወላጅና ድርጅቱ በግምገማው ማለቂያ ጊዜ ስምምነት ካላቸው ነው፣
- ወላጅ ልጁን በተደጋጋሚ ለግምገማ ከማምጣት ሲቀር ወይም እምቢ ሲል፣ ወይም
- የመንግሥት ድርጅቱና ወላጅ የ60 ቀን ግምገማ የጊዜ ገደቡን ለማራዘም ሲስማሙ።

የመጀመሪያ ግምገማ ላይ የ IEP ቡድን ልጁ ጉዳት አለበት፣ ልዩ ትምህርትና ተያያዥ አገልግሎቶች ያስፈልገዋል ብሎ ከወሰነ፣ የ IEP ቡድን የልጁን IEP ለማበጀት የመጀመሪያ ግምገማው ከመደረጉ ከ 30 ቀን በፊት መሰብሰብ አለበት። የመንግሥት ድርጅቱ ለወላጆቹ የ IEP ግምገማ ውሳኔ ግልባጭ ይሰጣቸዋል።

## ከሕጻናት መርሃ ግብር ወደ ልጆች መርሃ ግብር መሸጋገር፦

ከሕጻናትና ልጆች መርሃ ግብር እየተሸጋገረ ያለ ልጅ ልዩ ትምህርትና ተያያዥ አገልግሎቶች እንደሚያስፈልገው ለመወሰን፣ የመንግሥት ድርጅት የ IEP ቡድን ሰብስቦ መወያየት አለበት። ልጁ ከዚህ በፊት Part C ሥር አገልግሎት ያገኝ ከነበረ፣ አገልግሎቶች ያለምንም ችግር መተላለፍ እንዲችሉ፣ የ Part C አስተባባሪ ወይም ተወካዮች የመጀመሪያው ግምገማ IEP ስብሰባ ላይ እንዲገኙ፣ በወላጅ ጥያቄ መሠረት ጥሪ ይላካል። የ IEP ቡድን ልጁ ጉዳት እንዳለው ወይም የእድገት መዘግየት ያሳይ እንደሆነ ይገመግምና ለልጁ IEP ያወጣል። የልጁ IEP ሥራ ላይ መዋል ያለበት የልጁ ሶስተኛ ዓመት ልደት ላይ መሆን አለበት።

## ደግሞ ግምገማ ማድረግ፦

የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተከሰቱ የመንግሥት ድርጅቱ ለእያንዳንዱ ጉዳት ያለው ልጅ ድጋሚ ግምገማ መኪያሄዱን ማረጋገጥ አለበት፦

- የመንግሥት ድርጅቱ ለልጁ የሚያስፈልጉት ትምህርታዊ እና ተያያዥ አገልግሎቶች፣ የትምህርት መሻሻልና የሥራ ውጤትን ጨምሮ፣ ድጋሚ ግምገማ ያስፈልገዋል ብሎ ሲወስን፣ ወይም
- የልጁ ወላጅ ወይም አስተማሪ ድጋሚ ግምገማ ይደረግልኝ ብሎ ጥያቄ ሲያቀርብ/ስታቀርብ።

ወላጅና የመንግሥት ድርጅቱ በሌላ ካልተስማሙ በስተቀር፣ ከአንድ ጊዜ በላይ ድጋሚ ግምገማ በዓመት ከአንድ ጊዜ በላይ መሰጠት የለበትም፣ መሰጠት ያለበትም ቢያንስ

በሶስት ዓመት አንድ ጊዜ ነው፣ ወላጅና የመንግሥት ድርጅቱ ድጋሚ መገምገሙ አስፈላጊ አይደለም ካላሉ በስተቀር። በተቻለ መጠን የመንግሥት ድርጅቱ የልጁ ድጋሚ ግምገማ ስብሰባና የልጁ ሌላ የ IEP ቡድን ስብሰባዎች አብረው እንዲሄዱ ማበረታታት አለበት። የ IEP ቡድን ነባር መረጃን፣ ከወላጆች የተገኘ መረጃን ጨምሮ፣ ክፍል ውስጥ የተደረጉ ግምገማዎችን፣ የስቴትና የአውራጃ ግምገማዎችንና ግንዛቤዎችን በሙሉ አይቶ የሚከተሉትን ለመወሰን ተጨማሪ መረጃ ማስፈለጉን ይወስናል፦

- ልጁ ልዩ ትምህርትና ተያያዥ አገልግሎቶች የሚያስፈልጉት ዓይነት ጉዳት ቀጥሎበት እንደሆነ፣
- ልጁ አሁን ያለው የትምህርት ውጤትና ተያያዥ የእድገት ሁኔታ፣ እና
- ልጁ በ IEP የተወጠነለትን ዓላማ ለማሳካትና ተገቢ ከሆነ አጠቃላይ የትምህርት ገበታው ላይ ለመሳተፍ ተጨማሪ ነገሮች ወይም ለውጦች መደረግ እንዳለባቸው።

የIEP ቡድን ተጨማሪ መረጃ ያስፈልጋል ብሎ ከወሰነ፣ ወላጆች በቅድሚያ እስከሚነገራቸውና የወላጅ ፈቃድ እስከሚጠየቅ ድረስ ግምገማዎች አይካሄዱም። የ IEP ቡድን ግምገማዎቹ እንዲደረጉ ከጠየቀበት ቀን እስከ 90 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ የ IEP ቡድን የግምገማዎቹን ውጤቶች ያያል። የ IEP ቡድን ተጨማሪ መረጃ አያስፈልግም ብሎ ከወሰነ፣ የመንግሥት ድርጅቱ ወላጆችን ይህንኑ ያሳውቃቸውና የውሳኔውንም ምክንያቶች ይገልጽላቸዋል። የመንግሥት ድርጅቱ ግምገማዎችን ዳግም ለማድረግ ግምገማዎች የመፈጸም ግዴታ የለበትም፣ የልጁ ወላጆች ካልጠየቁት በስተቀር።

## የአገልግሎቶች ፍጻሜ፦

አንድ የመንግሥት ድርጅት አንድ ልጅ ጉዳተኛ መሆኑ አብቅቷል ብሎ ከመወሰኑ በፊት በፌዴራልና በስቴት ደንቦች መሠረት ተማሪውን ደግሞ መገምገም አለበት። ይህ በድጋሚ የሚደረግ ግምገማ በ IDEA Part B መሠረት ከመደበኛ ዲፕሎማ የሚያስገኝ ምረቃ ምክንያት የልጁ ብቃት ከመፈጸሙ በፊት መደረግ የለበትም፣ ወይም በስቴቱ ሕግ መሠረት የነጻ ተገቢ የመንግሥት ትምህርት (FAPE) ለማግኘት የዕድሜ ገደብ ስለታለፈ መሆን የለበትም።

# የግል ትምህርት መርሃ ግብር ሂደት (IEP)፦

## የIEP ቡድን ስብሰባዎች፦

የመንግሥት ድርጅቱ የቡድን ሂደት ተጠቅሞ በ IDEA ሥር በተገለጸው መሠረት አንድ ተማሪ ጉዳት ያለበት መሆኑንና የሚያስፈልጉትን የትምህርት አሰጣጥ ዘዴዎች ይወስናል። እያንዳንዱ የመንግሥት ድርጅት ጉዳት ያለበት ተማሪ IEPው እንዲደራጅ፣ እንዲከለስ፣ እንዲስተካከልና የልጁን የትምህርት ምደባ ለመወሰን ስብሰባዎች የማነሳሳት ኃላፊነት አለበት። የእያንዳንዱ ጉዳት ያለበት ወላጅ ለልጃቸው የ IEP ቡድን ስብሰባ ሲካሄድ ሊነገራቸውና ከፈለጉም የመሳተፍ ዕድል ሊሰጣቸው

ይገባል።

ወላጆች የልጁን የትምህርት ምደባ የሚወስነው የ IEP ቡድን አባሎች ናቸው። የመንግሥት ድርጅቱ ወላጆች እንዲገባቸውና ማንኛውም የልጁን የትምህርት ምደባ የሚመለከት ውይይት ላይ እንዲሳተፉ ተገቢ ሙከራዎች ማድረግ አለበት፣ መስማት ለሚሳናቸው ወላጆችና እንግሊዝኛ የትውልድ ቋንቋቸው ላልሆኑ አስተርጓሚ ማቅረብን ጨምሮ።

አንዴ የ IEP ቡድኑ ልጁ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ያስፈልገዋል ብሎ ከወሰነ በኋላ፣ የ IEP ቡድኑ በ30 ቀን ውስጥ ስብሰባ አካሂዶ የልጁን IEP ማዘጋጀት አለበት። ወላጆች የ IEP ቡድን አባል እንደመሆናቸው መጠን የልጃቸውን IEP በማንኛውም ጊዜ ጠይቀው የማየት መብት አላቸው።

## ስብሰባዎች ውስጥ የወላጅ ተሳትፎ፡-

እያንዳንዱ የመንግሥት ድርጅት ጉዳት ያለበት ተማሪ አንዱ ወይም ሁለቱም ወላጆቹ እያንዳንዱ የ IEP ስብሰባ ላይ እንዲገኙ ወይም የመሳተፍ ዕድል እንዲያገኙ ለማድረግ ሙከራ ያደርጋል። ወላጆች መሳተፍ እንዲችሉ አስቀድሞ ይነገራቸዋል፣ ስብሰባዎቹም የሚካሄዱት ሁሉም በተስማሙበት ሰዓትና ቦታ ይሆናል። ማስታወቂያ የስብሰባው ጉዳይ፣ ሰዓት፣ ቦታና ተሳታፊዎቹ ማን እንደሆኑ መግለጽ አለበት። እንዲሁም ወላጆች ወይም የመንግሥት ድርጅቱ ከተስማሙ፣ ማስታወቂያው ሌሎች ተሳታፊዎችን፣ ማለትም ስለልጁ ልዩ እውቀት ያላቸው ወይም ባለሙያዎችን፣ ተዛማጅ አገግልግሎት ሠራተኞችን ጨምሮ የ IEP ቡድን ስብሰባው ላይ ይሳተፉ እንደሆነ መናገር አለበት። የማንኛውም ግለሰብ እውቀት ወይም ልዩ ሙያ የሚወሰነው ግለሰቡ የ IEP ቡድን አባል እንዲሆን በጋበዘው ቡድን (ወላጆች ወይም የመንግሥት ድርጅቱ) ይሆናል።

ጉዳተኛ ተማሪ ዕድሜው 14ዓመት ሲሆን ጀምሮ፣ ወይም ተገቢ ከሆነ ከዚያም ሲያንስ፣ ማስታወቂያው አንዱ የስብሰባ ዓላማ የመዛወሪያ አገልግሎቶች አስፈላጊነት የሚጠቅስ አረፍተ ነገር መፍጠር እንደሆነ መግለጽ አለበት፣ ድርጅቱም ተማሪውን ይጋብዘዋል፣ ሌላ መቅረብ ያለበት ድርጅትም ካለ ወኪል እንዲልኩ ማስታወቅ አለበት። አንድ የመንግሥት ድርጅት ሌላ የድርጅት ወኪል ከመጋበዙ በፊት የወላጅ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

የአንድ ልጅን IEP ለማዳበር፣ ለማየት ወይም ለመከለስ የሚደረግ ማንኛውም የ IEP ቡድን ስብሰባ፣ የልጁን የትምህርት ምደባ ጨምሮ፣ ከመደረጉ ከ አሥር (10) ቀን በፊት ማስታወቂያ መሰጠት አለበት። የሚከተሉትን ለመወያየት አስቸኳይ ስብሰባ ካልተደረገ በስተቀር፡-

- የእርማት ጉዳዮችን ለመወያየት፣
- ልጁ ጉዳት ያለበት ተማሪ ሆኖ በአሁኑ ጊዜ ምንም ዓይነት የትምህርት አገልግሎት እያገኘ ካልሆነ፣ የልጁን ምደባ ለመወሰን፣ ወይም
- ልጁ FAPE ማግኘቱን ለማረጋገጥ ሌሎች አስቸኳይ አስፈላጊ ነገሮች ማሟላት።

ማንኛውም ወላጅ መገኘት ካልቻለ፣ የመንግሥት ድርጅቱ ሌሎች መንገዶች ተጠቅሞ ወላጅ እንዲሳተፍ ያደርጋል፣ ማለትም የግል ወይም የኮንፈረንስ ስልክ ተጠቅሞ። የመንግሥት ድርጅቱ ወላጆችን እንዲገኙ ማሳመን ካልቻለ፣ ስብሰባው ያለ ወላጅ ሊካሄድ

ይችላል። የመንግሥት ድርጅቱ ወላጅን ለማሳተፍ ሞክሮ ካቃተው፣ የ IEP ቡድኑ ያለ ወላጅ ተሳትፎ የምደባ ውሳኔ ሊያስተላልፍ ይችላል። በእንደዚህ ዓይነት ጊዜ የመንግሥት ድርጅቱ ከወላጆቹ ጋር በሚስማሙበት ጊዜና ቦታ ለመወያየት ያደረገውን ሙከራዎች፣ ለምሳሌ ዝርዝር የስልክ ጥሪዎችና ውጤቶቻቸው፣ ለወላጆች የተላኩ ደብዳቤዎችና መልሶቻቸው እና ወላጆቹ ቤት ወይም ሥራ ላይ የሄዱበትን ዝርዝርና ውጤቶቻቸውን መዝግቦ መያዝ አለበት።

አንድ ስብሰባ ኦፊሲዬላዊ ያልሆኑ ወይም መርሃ ግብሩ ላይ የሌሉ የመንግሥት ድርጅት ሠራተኞችን ወይም አንዳንድ የመነጋገሪያ ርእሶችን ለምሳሌ የማስተማሪያ ስልት፣ የትምህርት ፕላን፣ ወይም በአገልግሎት አሰጣጥ በተመለከተ የልጁ IEP ውስጥ ያልተጠቀሱ ጉዳዮችን የሚያነሱ ውይይቶችን አይጨምርም። የመንግሥት ድርጅት ሠራተኞች ሃሳብ ማቅረቢያ የሚያዘጋጁበትን ወይም ወላጅ ላቀረበው ሃሳብ መልስ ለመስጠት በሌላ ጊዜ ይሰበሰባሉ እንጂ መዘጋጃ እንቅስቃሴዎችን ስብሰባ ላይ አይወያዩም።

## የIEP ቡድን፦

የIEP ቡድን ተሳታፊዎች፦

- የልጁ ወላጆች፣ አሳዳጊ ወይም የወላጅ ወኪል፣
- ከአንድ ያላነሰ የልጁ አጠቃላይ አስተማሪዎች፣ ልጁ የአጠቃላይ ትምህርት አካባቢ እየተሳተፈ ከሆነ ወይም ወደፊት የሚሳተፍ ከሆነ። ልጁ የአጠቃላይ ትምህርት አስተማሪ ከሌለው ወይም ዕድሜው ትምህርት ቤት ለመግባት ያልደረሰ ከሆነ፣ በዛ ዕድሜ ያሉ ልጆችን ለማስተማር ብቃት ያለው ግለሰብ፣
- ከአንድ ያላነሰ የልጁ ልዩ ትምህርት አስተማሪ፣ ወይም ተገቢ ከሆነ የልጁ አገልግሎት ሰጪ፣
- ለጉዳተኛ ልጆች የሚሰጥ ልዩ ትምህርት መስጠት ወይም መቆጣጠር የሚችልና አጠቃላይ የትምህርት ገበታውን የሚያውቅና የመንግሥት ድርጅት መረጃ በደንብ ያለው የመንግሥት ድርጅቱ ወኪል፣
- የትምህርት ውጤቶችንና ግምገማዎችን ማገናዘብ የሚችል ግለሰብ። ይህ ሰው ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የመንግሥት ድርጅት አባሎች ውስጥ ሊሆን ይችላል።
- ወላጆች ወይም የመንግሥት ድርጅቱ ከፈለጉ፣ ሌሎች ስለልጁ እውቀትና ልዩ ሙያ ያላቸው ግለሰቦች
- ተገቢ እስከሆነ ድረስና ወላጆች ፈቃድ ከሰጡ፣ የመንግሥት ድርጅቱ ከማንኛውም ለመሸጋገሪያ አገልግሎቶች የሚከፍል ወይም የመስጠት ኃላፊነት ያለበት ተሳታፊ የመንግሥት ድርጅት ወኪል መጋበዝ አለበት፣ እና
- ተገቢ ከሆነ ልጁ። የስብሰባው ዓላማ የሁለተኛ ደረጃ ዓላማዎች ለመወያየት ከሆነና እነዚህን ዓላማዎች ለመፈጸም የሚያስፈልጉትን የሽግግር አገልግሎቶች የሚመለከት ከሆነ ልጁ ይጋበዛል፣ የ IEP ቡድን ስብሰባ ላይ እንዲገኝና እንዲሳተፍም ይጠበቅበታል።

## የIEP ቡድን በቦታው መገኘት፦

የጉዳተኛው ልጅ ወላጅና የመንግሥት ድርጅቱ የአባሉ የትምህርት ክፍል ወይም ተዛማጅ አገልግሎቶች ስብሰባው ላይ የማይቀየር ካልሆነ ወይም የማይወያዩት ከሆነና መሳተፉ አስፈላጊ አለመሆኑን በጽሑፍ ከተስማሙ የ IEP ቡድን አባል ስብሰባው ላይ በሙሉ ወይም በከፊል መሳተፍ የለበትም።

የ IEP ቡድን አባል ከ IEP ስብሰባ በሙሉ ወይም በከፊል ያለመሳተፍ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፣ ውይይቱ የአባሉን የትምህርት ክፍል ወይም ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚመለከት ሆኖ፦

- ወላጅና የመንግሥት ድርጅቱ በጽሑፍ ሲስማሙ፣ እና
- ከስብሰባው በፊት መምጣት የለብህም የተባለው አባል በጽሑፍ አስተዋጽኦውን የ IEP ዝግጅቱ ውስጥ ለወላጅ ወይም ለ IEP ቡድን ካስገባ።

## የIEP ይዞታ፦

IEP የተዘጋጀው በ IEP ቡድን ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፦

- የልጁን የአሁን ጊዜ የትምህርት ውጤቶችና ሥራ የሚያብራራ መግለጫ፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፦
  - የልጁ ጉዳት እንዴት አጠቃላይ የትምህርት ተሳትፎውን ሊዛባ እንደሚችል (ማለትም ጉዳት ለሌለባቸው ልጆች የሚሰጠው ዓይነት ትምህርት)፣ ወይም
  - መዋለ ሕጻናት ላሉ ልጆች፣ ተገቢ ከሆነ፣ የልጁ ጉዳት እንዴት ልጁ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ከመሳተፍ እንደሚያግዱት፣
- መመዘን የሚቻሉ ዓመታዊ ዓላማዎች፣ የሚከተሉትን ማድረግ የሚያስችሉ የትምህርትና የአሠራር ዓላማዎችን ጨምሮ፦
  - ልጁ በጉዳቱ ምክንያት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ማሟላት፣ አጠቃላይ ትምህርት ላይ መሳተፍ እንዲችልና መሻሻል እንዲያሳይ፣ እና
  - በልጁ ጉዳት ምክንያት የሚያስፈልጉትን እያንዳንዱን ትምህርት ነክ ነገሮች ማሟላት።

- እልባቶች ወይም የአጭር ጊዜ ዓላማዎች።.
- ልጁ ዓመታዊ ዓላማው ላይ የሚያሳየው መሻሻል እንዴት እንደሚመዘንና እንዴት በየጊዜው ሪፖርቶች እንደሚድረጉ ማብራሪያ (ለምሳሌ በየሶስት ወሩ ወይም በተወሰነ ጊዜ የሚወጡ ሪፖርቶች፣ ከሪፖርታ ካርድ ጋር አብረው የሚወጡ) ይሰጣል።
- የልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንዲሁም ተጨማሪ እርዳታዎችና አገልግሎቶች፣ በተቻለ መጠን በሠራተኞች ክለሳ ላይ የተመሠረተ፣ ለልጁ ወይም በልጁ ስም ይሰጣል፣ የመርሃ ግብሩ መሻሻያዎች ወይም ለትምህርት ቤቱ ሠራተኞች ልጁ የሚከተሉትን ማድረግ እንዲችል የሚሰጡ ድጋፎችን

የሚተነትን ማብራሪያ፡-

- ዓመታዊ ዓላማዎቹን ለመፈጸም ተገቢ እንቅስቃሴዎች፣
- አጠቃላይ የትምህርት ሥርዓት ላይ ለመሳተፍና ለማሻሻል እንዲሁም ሌሎች ከትምህርት ውጪ የሆኑ እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሳተፍ፣ እና
- ሌሎች ጉዳት ካለባቸውና ጉዳት ከሌለባቸው ልጆች ጋር አብሮ ለመማርና ለመሳተፍ፣

- መደበኛ ትምህርትና እንቅስቃሴዎች ላይ ለምን ልጁ ጉዳት ከሌለባቸው ልጆች ጋር እንደማይሳተፍ ማብራሪያ፣
- የልጁን የትምህርት ውጤትና አሠራር ለመመዘን የስቴት እና የአውራጃ ፈተናዎች ለመውሰድ የሚያስፈልጉ የግል ልዩ ማረፊያ ቦታዎችን የሚገልጽ ማብራሪያ፣ እና
- የIEP ቡድኑ ከስቴት ወይም ከአውራጃ ውጤት መመዘኛ ፈተና ልጁ የተለየ ፈተና መውሰድ አለበት ብሎ ከወሰነ፣ ምክንያቱን የሚያብራራ መግለጫ፡-
  - ልጁ ለምን መደበኛ ፈተና ላይ መሳተፍ እንደማይችል፣ እና
  - በቦታው የተመረጠው ፈተና ለልጁ ተገቢ መሆኑን፣;
- አገልግሎቶቹና ለውጦቹ ይጀምራሉ ተብሎ የታቀደው ቀንና የብዛቱ ቁጥር፣ ቦታው እና የእነዚህ አገልግሎቶችና መሻሻሎች ርዝመት።

የመንግሥት ድርጅት ለአንድ ልጅ በ IEPው መሠረት ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ይሰጠዋል፣ IEPው ውስጥ የተጠቀሱትንም ዓላማዎች መፈጸም እንዲችል ሊረዳው ይሞክራል። ልጁ እነዚህን ዓላማዎች መፈጸም ባይችል የመንግሥት ድርጅት፣ አስተማሪ ወይም ሌላ ግለሰብ ተጠያቂ አይሆንም።

IDEA 2004 የአንድ ልጅ IEP ውስጥ የIDEA ደንብ ከሚጠይቀው በላይ ተጨማሪ መረጃ እንዲኖር አይጠይቅም፣ የ IEP ቡድኑም በአንዱ የልጁ IEP ሥር ያለ መረጃ በሌላ IEP ሥር እንዲጨመር አይጠይቅም።

ልጁ የተራዘመ የትምህርት አገልግሎቶች የሚያስፈልጉት ከሆነ IEPው ከመደበኛ የትምህርት ዓመቱ ውጪ የሚሰጡትን ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶቹን በግልጽ ማሳየት አለበት።

## የሽግግር አገልግሎቶች፡-

የሽግግር አገልግሎቶች የተቀነባበሩ እንቅስቃሴዎች ሲሆኑ ከትምህርት ቤት ውስጥ ወደ ትምህርት ቤት ውጭ እንቅስቃሴዎች ለመሸጋገር የተሠሩ ናቸው፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን፣ ሥራና ቴክኖሎጂ ትምህርትን፣ የተቀነባበረ ቅጥርን፣ የአዋቂ አገግልግሎቶችን፣ ራስን ችሎ መኖርን ወይም ማህበረሰብ ውስጥ መሳተፍን ጨምሮ። እነዚህ እንቅስቃሴዎች ልጁ ምን እንደሚያስፈልገው ታይቶ፣ የልጁን ፍላጎት መዝግቦ፣ የጥናት መስክ፣ ተዛማጅ አገግልግሎቶችና የማህበረሰብ እንቅስቃሴዎችን ይጨምራል።

- አንድ ልጅ 14 ዓመቱ ወይም ተገቢ ከሆነ ከዛ በታች ሲሆን ጀምሮ፣ IEP በየዓመቱ የሚያሻሽለው የልጁ የጥናት መስክ ላይ ያተኮረ የሽግግር አገልግሎት አቅርቦት

ማብራሪያ መያዝ አለበት።

- ልጁ 16 ዓመት ሲሆነው ጀምሮ፣ ወይም የIEP ቡድን ተገቢ ነው ብሎ ከወሰነ ከዛ በታችም ሲሆን ጀምሮና በየዓመቱ እየተሻሻለ፣ IEP የሚከተሉትን መያዝ አለበት፦
  - ተገቢ መመዘን የሚቻሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዓላማዎች በዕድሜ መሠረት የሚደረጉ የሽግግር ፈተናዎች ከስልጠና፣ ትምህርት፣ ሥራ እና ተገቢ ከሆነ ራስን ችሎ ስለመኖር ዘዴዎች ጋር የተያያዙ ዓላማዎች፣ እና
  - ልጁ ዓላማውን መፈጸም እንዲችል የሚረዱትን የሽግግር አገልግሎቶች (የጥናት መስኮቹን ጨምሮ)።
- የሽግግር አገልግሎቶች ለማቅረብ ያለው ግዴታ በስቴቱ ሕግ ሥር እንደ ጎልማሳ የተከሰሰ፣ የአዋቂ እሥር ቤት ውስጥ የገባና ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ማግኘት መቻሉ ከመፈታቱ በፊት የሚያበቃ ጉዳተኛ ተማሪን አይመለከትም።

## አፈጻጸም ባጭሩ፦

ብቃቱ ለሚያበቃ ልጅ፣ የመንግሥት ድርጅቱ የልጁን የትምህርት ውጤትና አሠራር ባጭሩ የሚያሳይ ማብራሪያ ይሰጠዋል፣ ይህም ልጁ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ለመፈጸም ማድረግ ያለበትን ያካትታል።

## ለልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ፈቃድ መስጠት፦

ጉዳተኛ ልጅ የመጀመሪያ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ከማግኘቱ በፊት የመንግሥት ድርጅት ከወላጁቹ የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት። ወላጁ ተረድቶ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንዲጀመሩ በጽሑፍ ፈቃድ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም የመንግሥት ድርጅቱ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ማቅረብ እንዲጀምር ፈቃድ ለጠየቀው መልስ ካልሰጠ የመንግሥት ድርጅቱ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች መስጠት አይችልም። ወላጅ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንዲሰጡ ለቀረበለት ጥያቄ ፈቃድ ካልሰጠ፣ የመንግሥት ድርጅቱ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች መስጠት <u>አይችልም</u>። ጉዳተኛ የሆነ ልጅ ወላጅ የመጀመሪያ ፈቃዱን አልሰጥም ካለ፣ የመንግሥት ድርጅቱ FAPE ባለማቅረቡ ሕግ ጥሷል አይባልም፣ የ IEP ቡድን ስብሰባ መጥራትም የለበትም ለተማሪውም IEP ማዘጋጀት የለበትም።

## ለልዩ ትምህርት አገልግሎቶች የተሰጠን ፈቃድ መሰረዝ፦

ከዲሴምበር 31 2008 ዓ.ም. ጀምሮ፣ ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ሕግ (Individuals with Disabilities Education Act (IDEA)) ወላጆች ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎት እንዲቀርብ የሰጡትን ፈቃድ እንዲሰርዙ መብት ይሰጣቸዋል፣ ይህም ልጃው ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ማግኘቱን እንዲያቆም ያደርጋል። ይህም የዩ ኤስ የትምህርት መምሪያ ለረጅም ጊዜ የተጠቀመውን ፍቺ ቢቀይረውም፣ IDEA የሚያተኩርበትን ወላጆች የልጆቻቸውን መብት የመከላከል ሚናቸውንና

መምሪያው እንደሚለው የወላጅ በልጃቸው ትምህርት ተሳትፎንና ምርጫን ማጠናከርን ይደግፋል።

የመንግሥት ድርጅቱ ለጉዳተኛ ልጅ የልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ማቅረብ ከጀመረ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ወላጅ <u>በጽሑፍ</u> ፈቃዱን መሰረዝ ይችላል። ከዚህ በኋላ የመንግሥት ድርጅቱ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች መስጠት መቀጠል <u>አይችልም</u>፣ ልዩ ትምህርቱንና ተዛማጅ አገልግሎቱን ከማቆሙ በፊትም ለወላጅ የጽሑፍ ማስታወቂያ መስጠት አለበት። የመንግሥት ድርጅት የመገላገያ ስብሰባን ወይም ችሎትን ተጠቅሞ ልጁ አገልግሎቶቹን እንዲያገኝ ስምምነት ማግኘት <u>አይችልም</u>። የመንግሥት ድርጅቱ FAPEን ለልጁ አላቀረበክም ተብሎ ሊከሰስ አይችልም፣ የ IEP ቡድን ስብሰባም ማድረግ የለበትም ልጁ ተጨማሪ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንዲያገኝ IEP ማውጣትም የለበትም። ወላጅ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንዳይቀጥሉ ፈቃዱን መሰረዝ ቢችልም፣ የመንግሥት ድርጅቱ የልጁን የትምህርት መዝገብ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንዳገኘ የሚያሳይ ካለበት የመሰረዝ ግዴታ የለበትም።

## <u>የIEP እድገት፣ ግምገማና ክለሳ፡-</u>

የአንድ ልጅ IEP በሚወጣበት፣ በሚገመገምበትና በሚከለስበት ጊዜ፣ የ IEP ቡድን የሚከተሉትን አይቶ ይመዘግባል፡-

- የልጁ ጠንካራ ጎኖችና ወላጆች የልጃቸውን ትምህርት ለማሻሻል ያለባቸውን ሃሳብ፣
- የመጀመሪያው ወይም በቅርብ የተደረገው የልጁ ግምገማ ውጤቶች፣
- ልጁ በትምህርት፣ በእድገትና በአሠራር በኩል የሚያስፈልጉት ነገሮች፣
- የስቴትና የአውራጃ ፈተና መርሃ ግብሮች ላይ የልጁ አሠራር ውጤቶች፣ ተገቢ ከሆነ፣
- ለንግግርና ለመግባባት የሚያስፈልጉ ነገሮች፣
- ልጁ የሚያስፈልጉት ረዳት የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችና አገልግሎቶች።
- የልጁ ልዩ ሁኔታዎች፣ ለምሳሌ፡-
  - የልጁ የራሱ ባህርይ ከመማር የሚያግደው ከሆነ ወይም ሌሎች ልጆችን የሚያግድ ከሆነ፣ ይህንን ችግር ለመፍታት ባህርያ ማሻሻያ ዘዴዎችንና ድጋፎችን መጠቀም፣
  - አንድ ልጅ የትውልድ ቋንቋው እንግሊዝኛ ካልሆነ፣ የቋንቋ ችግሮቹን ከ IEPው ጋር ማገናዘብ፣

– እይነ ስውር ወይም በደንብ የማይታየው ልጅ ከሆነ፣ በብሬል ትምህርት መስጠት፣ የአይነ ስውራን ስርዓተ ጽሕፈት መጽሓፎችንና ሌሎችም ነገሮችን፣ የ IEP ቡድኑ የልጁን የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ተገቢውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ከገመገመ በኋላ (ወደፊት ልጁ የአይነ ስውራን ስርዓተ ጽሕፈት መጠቀሙን ግምገማ ማድረግንም ጨምሮ) የአይነ ስውራን ስርዓተ ጽሕፈት ትምህርት ወይም የአይነ ስውራን ስርዓተ ጽሕፈትን መጠቀም ለልጁ ተገቢ አይደለም ብሎ ካልወሰነ በስተቀር፣ እና

– ልጁ መስማት የሚሳነው ከሆነ፣ ልጁ የሚግባባበትን መንገድ አጢነው፣ ከእኩዮቹና ከባለሙያ ሠራተኞች ጋር በቀጥታ በቋንቋው የሚግባባበትን መንገድ፣ የትምህርት ደረጃና የሚያስፈልጉት ነገሮች መሟላታቸው፣ በልጁ ቋንቋና መግባቢያ መንገድ ትምህርት መስጠትን ጨምሮ።

ከላይ የተጠቀሱት ታይተው፣ የ IEP ቡድን ልጁ FAPE ማግኘት እንዲችል የተለየ መሳሪያ፣ አገልግሎት፣ እርዳታ፣ መንቀሳቀሻ ወይም የመርሃ ግብር ለውጥ ያስፈልገዋል ብሎ ከወሰነ፣ የIEP ቡድን ይህንኑ የሚያብራራ መግለጫ የልጁ IEP ውስጥ መጥቀስ አለበት።

የ IEP ቡድን አባል የሆነ የልጁ አጠቃላይ አስተማሪ የልጁ IEP ሲወጣ መሳተፍ አለበት። ተሳትፎ የሚያካትተው የባህርይ ለውጥ ግምገማ ሲደረግ፣ ተጨማሪ ረዳት መሳሪያዎች ለሃሳብ ሲቀርቡ፣ የመርሃ ግብር ለውጦችና ሌሎች የትምህርት ቤት ሠራተኞች ረዳቶችን ነው።

የIEP ቡድን የልጁን IEP የሚከተሉትን ለማድረግ በየጊዜው ማለትም በዓመት ከአንድ ጊዜ ባላነሰ ያየዋል፦

• የልጁ ዓመታዊ ዓላማዎች እየተፈጸሙ መሆናቸውን ለማየት፣ እና
• IEPውን እንደገተገቢነቱ እንደገና መከለስ፣ የሚከተሉትን ለማረም፦
    – ተገቢ ከሆነ፣ የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓት ላይ የዓመት ዓላማዎችን ለመፈጸም ምንም ዓይነት ጥረት ካልታየ፣
    – ማንኛውም በድጋሚ የተደረገ ግምገማ ውጤት፣
    - ስለልጁ መረጃ ለወላጅ ወይም ከወላጅ ተሰጥቶ፣
    – ልጁ የሚያስፈልገው ነገሮች፣ ወይም
    – ሌሎች ከልጁ መርሃ ግብር ጋር የተያያዙ ጉዳዮች።

## ማሻሻያ ነጥቦች፦

የልጁ ወላጆችና የመንግሥት ድርጅቱ IEPውን ለመቀየር የ IEP ቡድን ስብሰባ መጥራት ይችላሉ። ዓመታዊው የ IEP ስብሰባ ከተደረገ በኋላ IEPውን ለመቀየር፣ የጉዳተኛው ልጅ ወላጅና የመንግሥት ድርጅቱ የልጁት IEP ለመቀየር ወይም ለማሻሻል የጽሑፍ ሰነድ ለማዘጋጀት ሊስማሙ ይችላሉ። ወላጅ ጥያቄ ካቀረበ የተሻሻለው IEP ግልባጭ ሊሰጠው ይችላል።

## ምደባ፦

ወላጆች የ IEP ቡድን አባል እንደመሆናቸው፣ በልጃቸው ምደባ ውሳኔ እንዲገቡ ይደረጋል። በተቻለ ከፍተኛና ተገቢ መጠን የአእምሮና የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች፣ በሕዝብ ወይም በግል ተቋማት ወይም በሌሎች ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች ያሉትንም ተማሪዎች ጨምሮ የአእምሮና የአካል ጉዳት ከሌላቸው ተማሪዎች ጋር ይማራሉ። በየዓመቱ የሕጻኑ IEP ቡድን የሚከተለውን ያደርጋል፦

• በ IEPው ላይ በመመሥረት የሕጻኑን የትምህርት ምደባ ይወስናል፣ እንዲሁም
• የሕጻኑ IEP ሌላ ዝግጅት ካላስፈለገው በስተቀር ሕጻኑ የአእምሮና የአካል ጉዳት

ከሌለው በተመደበለት ትምህርት ቤት መማሩን ያረጋግጣል።

በስቴቱ ሕግ መሠረት ሕጻኑ በጎልማሳነት ተፈርዶበት በጎልማሶች ጠባይ ማረሚያ አገልግሎት እንዲቆይ/እንዲታሠር ከተፈረደበት እና ስቴቱ በቅን ልቦና ለመደረጉ ዋስትና ከሰጠ ወይም በሌላ በኩል ተቀባይነት ሊኖረው የማይችል አሳማኝነት ያለው የእሥር ቤት ተሃድሶ ካሳየ የ IEP ቡድኑ የሕጻኑን IEP ወይም ምደባ ሊያስተካክል ይችላል።

## <u>IEPን ተግባር ላይ ማዋል፦</u>

*የመንግሥት ድርጅቱ ማረጋገጥ ያለበት፦*

- ስብሰባው በበጋው ወራት ወይም በዝግ ወቅት፣ ወይም አጭር መዘግየትን የሚያስከትሉ ሁኔታዎች እንደመጓጓዣ ዝግጅትን የመሰሉ ካላጋጠሙ በስተቀር የሕጻኑ IEP በተቻለ ፍጥነት ወዲያው እንደተዘጋጀ ይተገበራል።
- IEP ለሕጻኑ በትምህርት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ሥራ ላይ ይውላል።
- IEPውን ለሁሉም አስተማሪ ለተዛማጅ አገልግሎት አቅራቢ እና ሌላ የልጁን IEP ለመተግበር ኃላፊነት አገልግሎት አቅራቢ በቀላሉ እንዲያገኙት ይደረጋል።
- እያንዳንዱ ለልጁ አገልግሎት እንዲሰጥ የተመደበ ግለሰብ የልጁን IEP ከመተግበር ጋር በተያያዘ ያለባቸውን ኃላፊነቶች እና መቻቻሎችን መስተካከሎችን እና መስጠት ስላለባቸው ድጋፎች መረጃ/መግለጫ መስጠት አለበት።
- ወላጆች የልጃቸው IEP ኮፒ ካለምንም ክፍያ ይደርሳቸዋል።

## <u>ወደ ሌላ የመንግሥት ድርጅት ስለሚዛወሩ ልጆች፦</u>

*በአንድ ስቴት ውስጥ የሚደረግ ዝውውር፦*

*የአእምሮና የአካል ጉዳት ያለበት ልጅ የመንግሥት ድርጅቶችን <u>በዚያው</u> የትምህርት ዓመት ውስጥ የሚለውጥ፣ ሌላ ስቴት ውስጥ የተተገበረ IEP ያለው አዲስ የመንግሥት ድርጅት ውስጥ የሚመዘገብ ከሆነ የመንግሥት ድርጅቱ፦*

- ለሕጻኑ ቀደም ሲል በተያዘው IEP ውስጥ የተገለጸውን አገልግሎት ያካተተ ነጻና ተገቢ የመንግሥት ትምህርት እንዲያገኝ፣ ይህንንም ከወላጆች ጋር በመመካከር የመንግሥት ድርጅቱ ቀድሞ የተያዘውን IEP እስኪቀበል የሚሠራበት ይሆናል፣ ወይም
- ከፌዴራልና ከስቴት ሕጉ ጋር የሚጣጣም IEP ማደራጀት መቀበልና ተግባራዊ ማድረግ።

<u>በዚያው</u> ስቴት ውስጥ ለሚዛወር ልጅ የሚመዘገብበት አዲሱ የመንግሥት ድርጅት የተማሪውን መዝገብ ከቀድሞው የመንግሥት ድርጅት ለማግኘት ተገቢና ወቅታዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ እነዚህም፦

- IEPውንና ድጋፍ ሰነዶችን፣ እና
- ለልጁ የተለየ ትምህርት ወይም ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚያመላክቱ ሰነዶችን

## ከስቴቱ ውጪ የሚደረጉ ዝውውሮች፦

የአእምሮና የአካል ጉዳት ያለበት ልጅ የመንግሥት ድርጅቶችን በዚያው የትምህርት ዓመት ውስጥ የሚለውጥ፣ ሌላ ስቴት ውስጥ የተተገበረ IEP ያለው አዲስ የመንግሥት ድርጅት ውስጥ የሚመዘገብ ከሆነ የመንግሥት ድርጅቱ፦

- ልጁ በቀድሞው IEP ውስጥ የተገለጹ አገልግሎቶችን ያካተተ ነጻና ተገቢ የመንግሥት ትምህርት እንዲያገኝ ከወላጆች ጋር በመመካከር ለመንግሥት ድርጅቱ አስፈላጊነቱ የታመነበት ግምገማ ማካሄድ እና
- ተገቢ ከሆነ ከፌዴራልና ከስቴት ሕግ ጋር የሚጣጣም አዲስ IEP ማደራጀት

ከስቴቱ ውጪ ለሚዛወር ሕጻን፣ ልጁ የተመዘገበበት የበፊቱ የመንግሥት ድርጅት ከአዲሱ የመንግሥት ድርጅት ስለትምህርት ሰነዶች የሚቀር ጥያቄዎችን ለማስተናገድ ተገቢ እርምጃዎችን በመውሰድ አገልግሎት ይሰጣል።

## የምረቃ አስፈላጊ ጉዳዮች፦

የመንግሥት ድርጅቶች ስለስቴቱና ያካባቢው ምረቃ አስፈላጊ ጉዳዮችና ልጃቸው እነዚህን ለማሟላት ስለደረሰበት ሂደት ለወላጆች ያሳውቃል። አንድ የአእምሮና የአካል ጉዳተኛ ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በመደበኛ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ሲመረቅ የመንግሥት ድርጅቱ ለወላጆቹ ስለልጃቸው መጪ ምረቃ ያሳውቃል። የመደበኛ ሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ ምረቃ የምደባ ለውጥንና የልጁን የ FAPE መብት ማብቂያ ያረጋግጣል።

## የተራዘመ የትምህርት ዓመት አገልግሎቶች (ESY)፦

የትምህርት ዓመት አገልግሎቶች መራዘም (ESY) ማለት የግለሰቡ የተለየና ልዩ ትምህርት እና የተዛማጅ አገልግሎቶች በ IEP መሠረት ለወላጆች ወጪ የሌለውና የ MSDE ደረጃን የጠበቀ አገልግሎት ለአእምሮና አካል ጉዳተኛ ተማሪ ከመንግሥት ድርጅቱ መደበኛ የትምህርት ዓመት ውጪ የሚሰጥ አገልግሎት ነው። የESY አገልግሎቶች ለ FAPE የሚያስፈልጉት አንድ የአእምሮና የአካል ጉዳተኛ ተማሪ በመደበኛ የትምህርት ዓመት የሚያገኛቸው ጥቅማ ጥቅሞች ትርጉም ባለው መንገድ ሲደናቀፉና ተማሪው በበጋው ወራት የትምህርት ፕሮግራም ሳይደርሰው ነው። የመንግሥት ድርጅቱ የ ESY አገልግሎቶችን ለተወሰኑ የጉዳት ምድቦች ሊገድብ አይችልም ወይም በራሱ ዓይነቱን፣ መጠኑን ወይም የአገግልግሎት ዘመኑን ሊወስን አይችልም።

የESY አገልግሎቶች የሚሰጡት የሕጻኑ IEP ቡድን በግለሰብ ደረጃ አገልግሎቶቹ ለ FAPE አስተዋጽኦ እንደሚያስፈልጉ ሲወስን ነው። ጉዳተኛ ተማሪው የሚያስፈልጉት ልዩ ነገሮችን ለማሟላት የሚያስችሉ የ ESY አገልግሎቶች እንዳሉ ወላጆች ይነገራቸዋል። ቢያንስ በየዓመቱ የ IEP ቡድን ተማሪው የESY አገልግሎቶች ያስፈልጉት እንደሆነ ይገመግማል። ይህ ግምገማ መደረግ ያለበት የትምህርት ዓመቱ

ሲጀመር ቀደም ብሎ፣ የመንግሥት ድርጅቱ ባቀረበው ሃሳብ ወላጆች ካልተስማሙ የመከላከያ መብቶቻቸውን ለማስከበር በቂ ጊዜ እንዲኖራቸው ነው። ሆኖም በጣም በጊዜ ሆኖ በቂ መረጃ ሳይኖረው ቀርቶ ውሳኔ መደረግ የለበትም።

ጉዳተኛ ተማሪ በበጋ ወራት ትምህርት ባይሰጠው በመደበኛ የትምህርት ዓመት ጊዜ የሚያገኛቸው ጥቅማጥቅሞች አለመስተጓጎላቸውን ለማየት የ IEP ቡድን የሚከተሉትን ያገናዝባል፦

- የልጁ IEP ውስጥ ያሉት ዓመታዊ ዓላማዎች አስፈላጊ የኑሮ ዘዴዎችን የሚያካትቱ መሆናቸውን፣
- በመደበኛው የእረፍት ጊዜ ልጁ የኑሮ ዘዴዎችን በተመለከተ ከፍተኛ ወደኋላ መሄድን የሚያሳይ ከሆነና እነዚህን ዘዴዎች በጊዜ መልሶ ማግኘት የማይችል እንደሆነ፣
- ልጁ የ IEP ዓላማዎችንና ግቦችን ለመምታት ጥሩ ሂደት ላይ ነው ወይ፣
- አዲስ ችሎታዎን ወይም ትልቅ ለውጥ የሚያመጡ ልዩ ዕድሎች አሉ ወይ፣
- እንቅፋት የሆኑ ባህርዮች፣
- የጉዳቱ ተፈጥሮ እና/ወይም ክብደት፣ እና
- ልዩ ገጠመኞች።

ልጁ ከመርሃ ግብሩ የትምህርት ጥቅም የማግኘት ችሎታው ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተጽእኖ ለማየት የ IEP ቡድን እያንዳንዱን ሁኔታ ለየብቻ ማየት አለበት። የ ESY አገልግሎቶች አስፈላጊ መሆናቸውን ለመወሰን ይሄ መለኪያ ለእያንዳንዱ ተማሪ በግል ደረጃ መደረግ አለበት። የተራዘመ የትምህርት ዓመት አገልግሎቶች ባለማግኘቱ ተማሪው በመደበኛ የትምህርት ዓመት ውስጥ የሚያገኛቸው ጥቅማጥቅሞች መዛባት አለመዛባታቸውን ለመወሰን የIEP ቡድን የሁኔታዎቹን ግምገማና ውጤታቸውን በሰነድ ማስቀመጥ አለበት።

ይህ ህትመት የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ፣ የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ነው። የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል ሥራ ቅጥርን ወይም በአንዳንድ የመርሀ-ግብር ተሳትፎዎችን በተመለከተ ተጸዕኖ ሊያሳድር የሚችል በጎሳ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በዕድሜ፣ በብሄር፣ በሃይማኖት ወይም በአካለ ስንኩልነት ላይ የተመሠረተ ምንም ዓይነት አድሎ አያደርግም። የክፍሉን አመራር በተመለከተ ጥያቄዎች ካልዎት የእኩልነት ማረጋገጫና መፈጸሚያ ቅርንጫፉን (Equity Assurance and Compliance Branch) በስልክ ቁጥር 410-767-0246 በመደወል ወይም በፋክስ ቁጥር 410-333-2226 ወይም መስማት ለሚሳናቸው በስልክ ቁጥር 410-333-6442መገናኘት ይችላሉ። ይህ ሰነድ ከዩ.ኤስ. የትምህርት ክፍል የልዩ ትምህርትና የመቋቋሚያ አገልግሎቶች በተገኘ ገንዘብ፣ በልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች፣ IDEA ክፍል B ችሮታ #HO27A060035A መሠረት ዳብሮና ታትሞ የተዘጋጀ ነው። እዚህ ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የግድ የዩ ኤስ የትምህርት መምሪያ ወይም የማንኛውም ሌላ የፌዴራል ድርጅት አስተያየቶች አይደሉም፣ እንደዛ መታየትም የለባቸውም። ይህ መረጃ ከሕትመት ሕግ (ኮፒራይት) ነጻ ነው። አንባቢዎች አባዝተው እንዲጋሩት ይበረታታሉ ሆኖም ከሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ገላጋይ አገልግሎቶች መምጣቱን እባክዎን ያስታውቁ። የአካል ጉዳት ያለባቸው አሜሪካዊያን (Americans with Disabilities Act (ADA)) በደነገገው መሠረት ይህ ሰነድ በተጠየቀ ጊዜ በአማራጭ አቀራረቦች ዝግጁ ሆኖ ይገኛል። የ Family Services and Interagency Branchን በስልክ ቁጥር 410-767-0858 ወይም በፋክስ 410-333-1571 ወይም መስማት ለሚሳናቸው በ410-333-0731 በመደወል ይገናኙ።

Maryland State Department of EducationDivision of Special Education/Early Intervention Services200 West Baltimore Street, 9th floorBaltimore, MD 21201 410-767-0261 ስልክ • 1-800-535-0182 የነጻ ስልክ 410-333-8165 ፋክስ • 410-333-0731 መስማት ለሚሳናቸው www.MarylandPublicSchools.org ናንሲ ኤስ ግራስሚክ፣ የስቴት ትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ፣ ጄምስ ኤች ደግራፈንራይድት፣ ጁኒየር፣ ፕሬዝደንት፣ የትምህርት ስቴት ቦርድ ካሮል አን ሂዝ-ባግሊን፣ ረዳት ስቴት ተቆጣጣሪ፣ የልዩ ትምህርት/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ክፍል፣ ማርቲን ኦማሊ፣ አስተዳዳሪ